# በምዕራብ አርሲ ዞን የሲንቄ ባህላዊ የህግ ስርአት እና የሴቶች መብት ጥበቃ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

የትናየት ደሳለኝ

ኢሳያስ አየለ

መስፍን እሸቱ

1. የሲንቄ ባህላዊ ሕግ የሚሰጡትን አገልግሎት እና ተቀባይነት ከግምት በማስገባት የባህላዊ ህጎችንና የባህላዊ ተቋማትን አሰራር በተመለከተ ዝርዝር ሕግ በሕግ አውጪው አለመውጣቱ በአፈፃጸም ረገድ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ በመሆኑም የሕግ አውጪው አካል አፈጻጸሙን በሚመለከት ዝርዝር ሕግን በማውጣት ይህን ችግር ሊፈታው ይገባዋል፡፡
2. ከዚህ በፊትም ሆነ ወደ ፊት በባህላዊ ህግ ዙሪያ ለተደረጉት እና ለሚደረጉት ጥናቶች የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተለይም በዚህ በኩል የትኞቹ የባህላዊ ሕጎች እና ተቋማት ናቸው ከሴቶች አንጻር ጠቃሚዎቹ? ህገ መንግስቱ ካስቀመጣቸው የሴቶች መሰረታዊ መርሆች ጋር ተጣጥመው መሄድ የሚችሉት እንዴት ነው? ባህላዊው የሲንቄ ሕግ እና የፍትህ ሥርዓት እንዴት ሊመጋገቡ ይችላሉ? ወዘተ… የሚሉትን በስፋት መርምሮ ጠቃሚ የሚባሉትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. ግጭቶችን አስቀድሞ የመከላከል እና ሲከቱም በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሚሆነው የህዝብ ተሳትፎ ሲኖር ነው፡፡ የማህበረሰቡ ወይም የህዝቡ ተሣትፎ መኖር በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃትና የመብት ጥሰት ለመቀነስ አይነተኛ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን በየደረጃው ያሉ የፖለቲካው ሥርዓትና የመደበኛው የፍትሕ አካላት ግጭቶችን እንዴት መከላከል እና መቆጣጠር ብሎም መፍታት እንደሚቻል በግጭት ፈቺነት ከሚሳተፉት የሀገር ሽማግሌዎች ምክር የሚያገኙበትን አደረጃጀት፣ መዋቅር እና አሰራር መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡
4. እያንዳንዱ ግጭት የራሱ ባህርይና መንስዔ እንዳለው በመረዳት ከግጭቱ ዓይነትና ከህዝቡ ባህል አንፃር እየታየ ከአካባቢው ባህላዊ ግጭት መፍቻ ተቋማት ጋር በህብረት በመስራት ግጭቶችን የመፍታት ልምድ ይበልጥ የሚዳብርበትን ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
5. የሲንቄ ባህላዊ የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓት አሁንም በአገልግሎት ላይ የሚገኙ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ

ግን በተለያዩ ምክንያቶች እየተዳከሙ በመሆናቸው መንግሥትና የሚመለከተው አካል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

6. መንግስት የብሔር ብሔረሰቦች ባህሎችን የማሳደግና የመንከባከብ ኃላፊነቶችን በመደገፍና በማበረታታት ላይ የሚገኝ በመሆኑ የባህል ቢሮዎችን በማደራጀት በክልሉ የአባ ገዳ ቢሮዎችን በመክፈትና በማደራጀት ሴቶች ጥቃትን እና የመብት ጥሰትን በባህላቸው መሰረት እንዲፈታላቸው የመደገፍ እና የማበረታታት ስራ በመስራት የመደበኛውን ፍርድ ቤት ላይ የሚደርሰውን የስራ ጫና በመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ ይህን አሰራር አቀኛጅቶ የሚሰራበትን አሰራር መፈጠር አለበት፣
7. ለትውልድ ባሕላዊ ሕጉን ለማስተላለፍ አሁን ያለበት ሁኔታ በቃል /በትውፊት/ ብቻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለታሪክ እና ለትውልድ መተላለፍ ያለበት በመሆኑ ተጽፎ የመታተም፣ የመሰራጨት እና ግንዛቤ የመስጠት ስራ ቢሰራ አሁን ያለውን ክፍተት ለመቀነስ ይቻላል